# “የስዩ አብርሃ ሚስጥሮች”

## የተስፋዬ ገብረአብ የመጻሕፍት-ሂሱ ሂስ



**በዘውገ ፋንታ**

መስከረም 2003

zegfantam@aol.com

*መግቢያ*

ደራሲው ተስፋዬ ገብረአብ ሰየ አብርሃ ስለጻፈው “ዝባዝንኬ” መጽሐፍ ባቀረበው “የመጻፍት-ሂስ” ሌላ ሂስ መጻፍ ለማይቀርብ ምግብ እጅ ማስታጠብ ይሆናል። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ተስፋዬ ገብረአብ ስለ ስየ መጽሐፍ ማሾፉን ለመቃወም ወይም ሰየን ለመደገፍ አይደለም። ስየ ይህን ከጠበቀ በውጤቱ ሊበሳጭ ይችላል። ተስፋዬ ገብረአብም የስየ መጽሐፍ ውሸት የዋጠው ነው ያለውን ይህ ጸሐፊ ቢደግፍም የዚህ ጽሑፍ ዓላም ሲገለጽ የሚያረካው አይሆንም። ስየ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያውቀው ከባድ ምስጢር አለኝ የሚለው ጉዳይ ተስፋዬ ገብረአብን ቢከነክነውም ይህ ጸሐፊ በዚህ ላይ የስየን አቋም ይቀበላል። ተስፍዬ ከስየ እጅግ ዝቅ ባለ ስልጣን ላይ ስለነበር፣ ስየ በሚስጥር የሰራውንና የሚያውቀውን ሁሉ አውቃለሁ ማለቱ ይህ ጸሐፊ አይቀበልም። ተስፋዬ በስየ መጽሐፍ ላይ የሰጠውን አስቂኝ ትችት በተለይ ስለ ሰፈሩት የውሸት ቃሎቹ እና ስለዝባዝንኪነቱ መቀበል ይቻላል። ይህ ጽሑፍ ስለ ተስፋዬ ገብረአብ ከንቱ አስተሳሰብ እንጂ ስለ ስየ መጽሐፍ ቁምነገር ወይም ‘ዝባዝንኬ’ ላይ ያተኮረ አይደለም።

የተስፋዬ ገብረአብ ሂስ

ከተስፋየ *የመጽሐፍት-ሂስ* ብዙ ስህተቶች ተለቅመዋል። ለዚህ ሂስም የበቀው የጉድለቱ ብዛትና ጥብቀት ነው። ተስፋየ ገብረአብ በዚህ አስተሳሰብ ሂሱን ይጀምራል፣ *“ሰዬ አብርሃ የፃፈውን መጽሐፍ አነበብኩት። የተደጋገመውን ዝባዝንኬ እየዘለልኩ እንደምንም ጨረስኩት።”* ይህ አባባል ደክሞ ያቀረበውን *የመጻፍት-ሂስ* እንዳለ ውድቅ ያደርገዋል። ሂስ የሰጠበትን መጽሐፍ ከዳር እስከዳር አላነበብኩትም ማለት ምንም መጽሐፉን ለማጣጣል የተሰነዘረ አስተሳሰብ ቢሆንም፣ እውነትነትና አስፈላጊ የጽሑፍ ስነስርዓት የጎደለው መሆኑን መረዳት ይቻላል። ተስፋዬ የስየን መጽሐፍ ለማቃለል ሲል የሰነዘረው እራሱን በይበልጥ ዝቅ አድርጓታል። የተስፋዬ የመጽሐፍት-ሂስ በዚህ አቋም ተጀምሮ የተደመደመ ይመስላል፣ ስለሆነም ሰየ አብርሃ ስለመጽሐፉ የተሰጠው አቃቂር ይህን ሂስ ከተመለከት ፈካ ሊል ይችል ይሆናል። ዳሩ ግን፣ ቀጥሎ የቀረበው ጽሑፍ የሱን “ዝባዝንኬ” መጽሐፍ ለመደገፍ ወይም ለማወደስ እንዳልሆን ሲረዳ ደስታው ቶሎ ያልቃል። በጠቅላላው የተስፋዬ ሂስ እንዲሁ በተራው በዚህ ሂስ ተጣጥሎ ሲገለጽ ሁሉም የቀልድ ጋጋታ ይሆናል።

የመጻሕፍት-ሂሱ ሂስ

ተስፋዬ ገብረአብ ስለ ስየ ከበድ ያለ አስተያየት አለው። በዚህም የሚገረም ሰው ላይኖር ይችላል። ተስፋዬ ገብረአብ *አዞሮ ማየት* የሚባለውን ነገር እንዳልቃኘው ጽሑፉ ያመለክታል። ይህን የሚያመለክቱ ከጽሑፉ ብዙ ዐረፍተነገሮች አሉ። በአንዱ መስመር እንዲህ ይላል፤ *“ጥሩ አንባቢ ሆነህ ሳለም ታሪክህን የግድ ራስህ መፃፍ ላይኖርብህ ይችላል። ከፃፍክም ደግሞ ጥሩ አማካሪና አርታኢ መፈለግ ይገባ ይሆናል።”* ተስፋዬ እንዲህ ብሎ የስየን ንግግር ከጠቀሰ በኋላ ዘወር ብሎ፣ *“ቃል በቃል ባይሆንም ሰዬ*

*ይህን ይለናል።”* ብሎ ይደመድማል። ችግሩ፣ ስየን ጠቅሶ ካስቀመጠ በኋላ ቃል በቃል እንዳልሆነ መልሶ ማርዳቱ ወይም ማስረዳቱ ነው። ቀጥሎም፣ *“ጥሩ አንባቢ ያልሆነ ሰው ለመፃፍ ባይሞክር ይመረጣል።”* ይላል። ተስፋዬ ገብረአብ ጥሩ ጸሐፊ ነው። ግን የአጻጻፍ ስርዐቱ ሲመጠን ብዙ ግድፈት በጽሑፉ ውስጥ ይታያል። *አዙሮ ማየት* ትልቁ ችግሩ ይመስላል። ይህን አጉልቶ የሚያሳየው አስተሳሰብ፣ *“የሆነው ሆኖ የስየ አብርሃ መጽሐፍ ላይ ሂስ የማቅረብ ፍላጎት የለኝም። ጊዜም የለኝም። አንዳንድ ያስገረሙኝን ነጥቦች ብቻ በጨረፍታ ላነሳ ወደድኩ።”* የሚለው ዕውነተኝነት ያነሰው አስተያየት ነው። በጽሑፉ ይህን አስተያየት ሲሰጥ፣ የጽሑፉ ዐርእስት ግን ሙሉ የመጻፍት-ሂስ እንደሆነ የአንባቢ ልምዳዊ አስተሳሰብ ነው። ተስፋዬ ወርቃማ ጊዜውን በከንቱ አባክኖ የአንባቢውን ጊዜ ማባከኑን ጠቅሷል። ይህ ቦታ የሌለው ቁንጭል አስተሳሰብ ነው። ይህን አባባል በመዘንጋት፣ *“በገፅ 155 ላይ ታዲያ የራሱን አባባል እንዲህ ሲል ያፈርሰዋል።”* በማለት ስየ ስለ አደረገው የሃሳብ መገለባበጥ ያመለክተናል። ተስፋዬ ገብረአብ አዙሮ የማየት ጣጣ እንዳለበት አድምቆ ያሳያል። ስለደጋገመውም የሰከነ ልምዱ ነው ብሎ ለማሰብ ያበቃል። ሌላ ማስረጃም ከጽሑፉ ጎልጎል ማውጣት ይቻላል። ደራሲ ተስፋዬ *“እየነጠርኩ”* አለፍኩት በማለት ከስየ *መጽሐፍ* ብዙ ያላነበበው ክፍል እንዳለ ካመለከተ በኋላ፣ ደራሲው ስዩ በውሸት የጻፈውን ከየገጹ እየለቀመ አቅርቧል። ይህ ከሆነ፣ ተስፋዬ የስዬን *መጽሐፍ* ከዳር እስከ ዳር አንብቧል ወይስ *“እየነጠረ”* የስህተቱን ገጽና ዐረፍተነገር ብቻ በአንድ ዘዴ እያገኘ ስለመጽሐፉ ሙሉ ሂስ አቅርቧል የሚያሰኘውን አስተሳሰብና ግምት ለአንባቢ መተው ተገቢ ይመስላል።

ተስፋዬ ገብረአብ ስለ ስየ ውሸት በማያጠያይቅ ሁኔታ በድርጊቶች አማካይነት እያመሳከረ አቅርቧል። ይህን ለማድረግ የስየ ውሸቶች እረድተውታል። ተጨልፎና ተጠልቆ የማያልቅ የውሸት ባህር የወያኔ አካል የሆነ ሁሉ የመዋኛ ባኅሪው ስለሆነ፤ ስየን ለሚያውቅ ኢትዮጵያዊ አዲስ ዜና አይሆንም። ተስፋዬ ጠለቅ ብሎ ከቻለ አዲስ ነገር ቢያፈልቅና የስዬን ድብቅብቅ ሚስጥር ቢያጋልጥ ኖሮ ስየ አብርሃ እንኳን በአገር መሪነት መድረክ ቀርቶ በመንገድም ለመታየት የማይፈልግ ሰው ባደረገው ነበር። ዳሩ ግን፣ እንኳንስ ስየ ራሱ ተስፋዬ ገብረአብም ስለ ሚስጥር ጉዳይ መዘክዘክ ብዙ የቀራቸው እንጅ ያለቀባቸው አይመስሉም። በዚህ ላይ ተስፋዬ ሊያዘናጋን ሞክሯል።

ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ ስለ ፖለቲካ ወይም ሌላ ዓላምው ዘመሜታ የሰጠው ምልክት አለ። ተስፋዬ፣ *“በጦርነቱ የተቻላቸውን ሁሉ ሞክረዋል! ስላልተቻለም ተመልሰዋል!ሌላ ሰበብ ማብዛት ለምን አስፈለገ?”* ካለ በኋላ፣ ቀጠል አድርጎ፣ *“ውጊያውን በተመለከተ ወደፊት ይፋ የሚሆን ምንም እንቆቅልሽ የለም። ቢኖር እስካሁን እናውቀው ነበር። ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ ስየ የማያውቀው ምንም መረጃ የለም።”* ይለናል። ጉዳዩን ለመቋጨት፣ *“ስየ በመጽሐፉ ይህን በግልፅ ከመናገር ይልቅ አንድ ትልቅ የሚያውቀው ሚስጥር ያለ ለማስመሰል ሞክሯል።”* በማለት የሀሳብ ወይም የፖለቲካ አዝማሚያውን በዚህ ዐረፍተነገር ቁልጭ አድርጎ ያስቀመጠው ይመስላል። ስለ ጦርነቱ መጀመሪያና መደምደሚያው ምክንያት የምናውቀውን ሁሉ ተስፋዬ ከአእምሮአችን በድፍረት ሊሰርዘው ሞክሯል። በዚህ ላይ ተስፋዬ ገብረአብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ልብና ጀርባ ሳይሆን አልቀረም። ተስፋዬ ገብረአብ በዚህ *መጽሐፍት-ሂስ* ያሳየው የአስተሳሰብ ድክመት፣ የምርምር ዕጥረትና የፖለቲካ አዝማሚያነት የተጋለጠበት እንደሆነ አንባቢ ሊገነዘብ ይችላል። ጠ/ም መለስ ዘናዊ የሀገር ሚስጥርን አስመልክቶ ደራሲው ስየ አብርሃ እንደሚለው “ብዙ ሚስጥር አለ ግን አንናገረውም” ቢል ኖሮ ምናልባት ተስፋዬ ገብረአብ “የምን ሚስጥር? መለስ ሚስጥር የሚለው። ውሸት ነው፤ የደበቀው ሚስጥር የለም።” ሊል እንደሚችል አዝማሚያውን አንባቢ እንዲገምት አድርጎል። ስየ አብርሃ ከፍተኛ ባለሥልጣን ከሆኑት አንዱ መሆኑንና ፈላጭና ቆራጭ እንደነበረ እራሱ ተስፋዬ ደጋግሞ ተናግሯል። *ታዲያ* እንዴት ብሎ ተስፋዬ ስየ አብርሃም ሚስጥር

እንደሌለው አድርጎ የሚነግረን? ተስፋዬ ስየ የሚያውቀውን አውቅ ነበር ወይም ለማወቅ እችል ነበር የሚል ከሆነ በስለላ ደረጃ እንጂ ከስብሰባ ጠረጴዛ ዙሪያ አብሮ ተቀምጦ እንዳልሆነ የተጻፈው ሁሉ ያስረዳል። ስየ ሚስጥር የሚያውቅ መሆኑ ተስፋዬን እጅግ የከነከነው ጉዳይ መሆኑ ጎልቶ ይታያል። *"ይህን ሚስጥር፣ ይህን ስንክሳር፣ ይህን እንቆቅልሽ ወደፊት ታሪክ ያወጣዋል።" ሲል ፃፈ። ምንድነው ያ ሚስጥር?"* በማለት ተስፋዬ ተገርሞ ጽፏል። ስየ 'አትንኩን ከነካችሁን እናወጣዋለን' የሚለው አባባል አለ። ደራሲው ተስፋዬ ግን፣ "ስየ አብርሃ ያልነገረን ምስጥር የት ይሆን ተፈልጎ የሚገኝ?" ሲል ተማሮ ጽፏል። ለተስፋዬ ሚስጥር እንዴትና የት ተፈልጎ እንደሚገኝ ለመግለጽ ስለማይቻል 'ሚስጥር' መባሉም ለዚህ ነው። አለበለዚያ ግን፣ ስየ እራሱን የሚያስጠፋ ወይም ሕዝብን ከቀውስ ላይ የሚጥልና ሀገርን የሚያናጋ መጥፎ ድርጊት በሚስጥር የያዘ መሆኑን ሲነግረን አለማመኑ ይከብዳል። የስየን ቀድሞ ስልጣን ተረድቶ ማመኑ ይሻላል። ለተስፋዬ ከማመኑ አለማመኑ በልጦበታል። ዋናው ጉዳይ ግን ስየ በከፍተኛ አመራር ውስጥ የነበረ፣ ሁሉን ሚስጥራዊ ጉዳይ ሊያውቅና ከዚያም በላይ ምስጥራዊ ጉዳይ ሊፈጥርና ሊሰራ ይችል እንደነበር መገመት ለተስፋዬ ተስኖታል።

በስየ መሪነት ብዙ ዕቃዎችና መሳሪያዎች በሽሽግ በሌሊት ወደ ትግራይ እንደሚጓዙ ተስፋዬ ገብረአብ ከነማስረጃው ጭምር እያቀረበ ገልጿል። ዳሩ ግን እነ ስየ ይህን ዘረፋ የተማሩት ከሻቢያ እንደነበርና "ለከፈልነው ደም የሚገባን ድርሻችን ነው" የሚለውንም ፈሊጥ ከሻቢያ የተማሩት መሆኑ ዕውቅ ሲሆን፣ ተስፋዬ ወያኔንና ሻቢያን አጣምሮ ማየት የተሳነው ይመስላል። አንድ መንጋ ሆነው ሀገር የደመሰሱት አሁን እርስ በርሳቸው ሲካሰሱና ሲናቆሩ ማየቱ መጥፎ አይደለም። ገና በይበልጥ መፈነካከታቸው አይቀርም። ብዙ ሚስጥር ይወጣል፣ ተስፋዬ ገብረአብ እንደሚፈልገው አሁን ባይሆንም በኢትዮጵያ ሕጋዊ መንግሥትና አገዛዝ ሲቋቋም በተረጋጋና በስነሥርዐት ብዙ የሚናዘዝ ይፈልቃል፣ ብዙ መጥፎ ታሪክም ይጻፋል።

*መደምደምያ*

ተስፋዬ ገብረአብ በርግጥ ባለው የመጻፍ ችሎታ የስየን መጽሐፍ እንደሚገባው ቀልዶበታል። ስየ አብርሃ መጽሐፉም እሱም ምንጊዜም ለዘለፋ ምቹ ናቸው። ተስፋዬ እንዳለው ስየ ፍትሕ ፈላጊ ተበዳይ ሰው አይደለም። ምሕረት ጠያቂ ሰው ግን ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብና ሀገር ላይ ስለፈጸመው ወንጀል ሲጠየቅ "ሂሳብ ልናወራርድ" አልመጣንም የሚለው ዘይቤ አለ። ዕውነቱን ነው ሂሳብ ማወራረጃ ወቅቱና ጊዜው አሁን አይደለም። ስየ መሪ ለመሆን መጣሩ ዘመኑ እጅግ የተበላሸ መሆኑን ያሳያል። ስዬ ከመለስ ዜናዊ ያነሰ ኃጥያት ነው ያለኝ እና እሱ በዘውድ ላይ ከተቀመጠ እኔም ይገባኛል የሚል ይመስላል። አሁን ይህ አስተሳሰብ ትክክል ነው፣ ነገ ግን ዓለም ሲለወጥ ያሳፍራል። መለስ ነገ ይሂድ አዜብም ትንገስ ብርቱካንም ሌሎቹም ይፈቱ! በኢትዮጵያ ምድር ይህ የዛሬው ጧት ተባራሪ ሀሳብ ይመስላ። እንዳፋቸው! ነገ ደግሞ ሌላ ጥሩ ሀሳብ ይወለዳል።

ተስፋዬ ገብረአብ ያቀረበውን የመጻሕፍት-ሂስ በፈገግታ እንድናነብለት ሞከሯል፣ በመጨረሻም ይህን ቀልድ ጨምሮ ስለደመደመ ተሳክቶለታል፣ "መለስ ጮማውን እንዴት ለመዳችሁት ሲባል 'በመከራ!'" አለ አሉ ይለናል። መለስ አይልም አይባልም!